5ኛ ዓመት ቁጥር 41
4th year Nº. 41

ባህር ዳር ጳጉሜ 2 ቀን 1991 ዓ.ም
Bahir Dar 7th sept., 1999

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKR HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 2.45	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 p.O.BOX

ማ ው ጫ	CONTENT
አዋጅ ቁጥር 41/1991 የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገጽ 8	Proclamation Nº 41/1999 A Proclamation To Provide For The Reestablishemnt Of Rural Roads Authority Of The Amhara Natoinal Regional State Page 8

አዋጅ ቁጥር 41/1991
የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የገጠር መንገዶች መስፋፋት ለክልሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት መፋጠን ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ፣

የገጠር መንገዶችን ግንባታና ጥገና በቅልጥፍና ለማካሄድ የሚቻለው ራሱን በቻለ ጠንካራ ተቋም ሲመራ መሆኑን በመገንዘብ፣

የገጠር መንገዶች ባለስልጣንን እንደገና በአዲስ መልክ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

PROCLAMATION Nº 41/1999
A PROCALMATION TO PROVIDE FOR THE RESTABLISHMENT OF RURAL ROADS AUTHORITY OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

WHERE AS, realizing that the expansion of roads, to rural areas, has a great role in accelerating economic and social development of the region.

WHERE AS, it has been found that a rapid construction and maintenance of rural roads can effectively be carried out when it is managed by an autonomous strong institution.

WHERE AS, it has become necessary to reestablish the rural roads Authority.

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49/3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል::

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 41/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1."ገጠር መንገድ" ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 80/1989 በተሰጠው ሥልጣን "ገጠር መንገድ" ብሎ የሚሰይመው መንገድ ነው::

2. "መንግሥት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፣

3. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተጠቀሰ የአማራ ክልል ነው::

4. " ምክር ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው::

5. "የኮሚኒቲ መንገድ" ማለት ምክር ቤቱ በሚያወጣው ፖሊሲ መሠረት የየአካባቢው ህዝብ በገንዘቡና በጉልበቱ ወይም በዕርዳታ የሚሠራውና የሚጠገነው መንገድ ነው::

6. " ግንባታ" ማለት የኮንስትራክሽንና የማሻሻያ ተግባሮችን የሚያጠቃልል ተግባር ነው::

ክፍል ሁለት
ስለ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እንደገና መቋቋም ድርጅታዊ አቋምና ዓላማዎች፣

3. እንደገና ስለ መቋቋምና ተጠሪነት

1.የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን /ከዚህ በኋላ ባለሥልጣን እየተባለ የሚጠራ/ የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል::

2.ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል::

NOW,THERE FORE, in accordance with the constitution of the region article 49/3/1 the council of the ANRS proclaimed the following

PART ONE
GENERAL

1. Short title

This proclamation may be cited as the "Rural Road Authority of the Amhara National Regional State Reestablishment proclamation Nº 41/1999"

2. Definition

Unless the context requires other wise, in this proclamations:

1. " Rural Road" means rural roads to be designated as such by Ethiopian roads authority pursuant to the power vested in it by its reestablishment proclamation Nº 80/1998.
2." State" means the Amhara National Regional State
3. "Region" means the Amhara National Region Specified as such in article 47 of the Constitution of Federal Democratic Republic of Ethiopia.
4. "Council " means Council of the Amhara National Regional State.
5. " Community Road" means a Road constructed and maintained by the people of a certain environment with their own finance and labor or with assistance pursuant to a policy to be issued by the council.
6." Construction " means an activity encompassing construction and improvement.

PART TWO
Reestablishment, Organizational Structure, and Objectives

3 .Reestablishment and Accountability

1.The Rural Road Authority of the Amhara National Regional State here in after referred to as " The Authority" is here by reestablished as an autonomous governmental institution under this proclamation.

2.The Authority shall be accountable to the executive committee of the Amhara National Regional State.

306

306 ~~273~~ 306

3.የባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል። አንደ አስፈላጊነቱም ቅርንጫፍ መ/ቤቶችን በሌሎች ሥፍራዎች ማቋቋም ይችላል።

4.የባለሥልጣኑ መ/ቤት ድርጅታዊ አቋም

ባለሥልጣኑ፡-

1. አንድ የሥራ አመራር ቦርድ
2.በቦርዱ አቀራረብነት በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣
3.ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈልጉ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ይኖሩታል።

5.ዓላማዎች

የባለስልጣኑ ዓላማዎች፡-

1.የገጠር መንገዶችን ለማልማትና ለማስተዳደር እንዲሁም የገጠር መንገዶችን ግንባታ ሥራ ውጥኑን ለማረጋገጥ ይሆናል።
2. ህዝቡ በኮሚኒቲ መንገድ ግንባታና ጥገና በቀጥታ የሚሳተፍበትን አመቺ ሁኔታዎች ለማመቻቸት ይሆናል።

ክፍል ሶስት

የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም የስብስባ ሥርዓት

6. የቦርዱ መቋቋምና ተጠሪነት

1.የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ በክልሉ መንግሥት የሚሰየሙ ከ5 እስከ 7 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

2.የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላት መካከል በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰየም ሲሆን የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል።
3.የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን በክልሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይወሰናል።

7. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

1.ባለሥልጣኑ የሚያመነጫቸውን ክልላዊ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና መመሪያዎችን እንዲሁም የባለሥልጣኑን የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራሞችንና በጀት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ገምግሞ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል።

3.The Head office of the Authority shall be in Bahir Dar. Branch offices may be established in other places as may be necessary.

4.Organizational Structure

The Authority shall have:

1.a managing board.
2.a manager to be appointed by the executive committee.
3. other staffs necessary on each level.

5 .Objectives

The objectives of the authority shall be to:

1.Develope and administer rural roads and to verify the consistency of the construction of rural roads.
2.Facilitate conducive atmosphere for the participation of the people in the construction and maintenance of community roads.

PART THREE

Establishment, Meeting procedures, Powers and Duties of the Managing Board of the Rural Road Authority.

6.Establishemnt and Accountability of the Board

1.The board shall consist of 5 to 7 members to be assigned by the Regional state and shall be accountable to the executive committee of the Region
2.The chair person is going to be assigned from among the members by the executive committee, while the General Manager is to be its secretary.
3. The term office of the members of the Board shall be, decided by the executive committee.

7. Powers and Duties of the Board

The board shall have the following powers and duties to:

1.Evaluate and submit to the executive committee, regional polices, laws and directives as well as short and long term plans and annual work program and budget of the authority, initiated by the general manager and upon approval follow up the implementation of the same.

2.ገጠር መንገዶችን በሚመለከት መንግሥትና ክልሉ የሚያወጧቸው ፖሊሲዎች፣ ህጎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል::

3.ባለሥልጣኑ ለሥራው አፈጻጸም የሚያወጣቸውን ውስጠ ደንቦችና መመሪያዎች ያፀድቃል፣

4.ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ሥንብት ያፀድቃል፣ ሆኖም የመምሪያ ኃላፊዎችን ሹመት ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል::

5.በዋና ሥራ አስኪያጅ በሚቀርቡ ሌሎች ጉዳዩች ላይ ይወሰናል::

8.የቦርዱ ስብሰባ

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ ይደረጋል፣ ሆኖም በስብሳቢው ሲጠራ ወይም የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሲጠይቅ ቦርዱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል::

2.በቦርዱ ስብሰባ ላይ አብዛኞቹ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል

3.የቦርዱ ውሣኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምፅ ሲደገፍ ነው:: ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ስብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል::

4.የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

ክፍል አራት

የገጠር መንገዶች ባለሥልጣንና የዋና ሥራ አስኪያጅ ጠቅላላ ሥልጣንና ተግባር

9. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1.መንገዶችን የሚመለከቱ የመንግሥት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያስፈጽማል፣

2. ገጠር መንገዶችንና ኮሚኒቲ መንገዶችን የሚመለከቱ ክልላዊ ፖሊሲዎችን፣ሕጎችንና መመሪያዎችን ያመነጫል፣

3. ባለሥልጣኑን የሚመለከቱ ክልላዊ ፖሊሲዎችን፣ሕጎችንና መመሪያዎችን ያመነጫል፣ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

2.Ensure implementation of policies, laws and directives issued by the federal and the Regional state, concerning Rural Roads.

3.Approve internal regulations and directives to be issued by the authority for the performances of its activities.

4.Approve the employment, assignment and dismissal of heads accountable to the manager however it shall submit for approval the appointment of department heads to the executive committee.

5.Decide upon such other matters presented to it by the general manager

8. Meeting of the Board

1.The regular meeting of the board shall be held ones in every three months; provided, how ever, when the chair person calls or when the manager requests so, the board may hold extra ordinary meetings at any time.

2.The presence one of the majority of the members at any board meeting shall constitute a quorum.

3.Decisions of the board shall be passed by a simple majority vote; However, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4.With out prejudice to the provision of this article, the Board shall adapt its own rules and meeting procedures.

PART FOUR

General Powers and Duties of the Rural Road Authority and The General Manager

9. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the following powers and Duties to:

1. Cause the execution of policies and laws of the state regarding roads.

2. Initiate regional policies, laws and directives concerning Rural and community roads.

3. Initiate regional policies, laws and directives concerning the Authority as well as prepare short and long term plans and programs; and implement same upon approval

4.የገጠር መንገዶችን ፊዚቢሊቲ /አዋጭነት/ ጥናት ያካሄዳል፣ እንዲካሄድም ያደርጋል፣

4.Carry out and cause the carrying out of feasibility studies of rural Roads.

5.የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሚያወጣቸውን የዲዛይን ደረጃዎች በመከተል ለገጠር መንገዶች የሚያስፈልጉትን ዲዛይኖች በበቂ አማካሪዎች አማካይነት ወይንም በራሱ ያዘጋጃል።

5.Prepare, using qualified consultants, or by it's own designs for Rural Roads, in line with the standard design issued by Ethiopian road authority.

6.የገጠር መንገዶች ግንባታ በሥራ ተቋራጮች አማካይነት ወይም በራስ ኃይል ያካሄዳል። ሆኖም በገበያ ላይ ብቁ የሥራ ተቋራጮች መኖራቸው ሲረጋገጥ የግንባታ ሥራዎች በተቋራጮች እንዲካሄድ ያደረጋል።

6.Cosntruct rural roads by its own or by private constructors. Cause the construction of roads by private contractors, when the availability of efficient private contractors in the market is approved.

7.ገጠር መንገዶች በራሱ ኃይል ይጠግናል ወይም በሥራ ተቋራጮች ያስጠግናል።

7. Maintain Rural Roads or cause the maintenance of the same by its own force or private contractors.

8.የሥራና አማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይዋዋላል፣ ሥራዎች በውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል።

8.Prepare and cause the preparation of Construction and consultancy service contracts, enter in to contract and supervise to ensure the accomplishment of the same is in accordance with the standard set for in the contract.

9.ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 80/1989 የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የገጠር መንገዶችን የዲዛይን፣ የኮንስትራክሽንና የቁጥጥር ሥራዎች ለዓለም አቀፍ የውጭ ተቋራጮችና አማካሪዎች ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ያስፈፀማል።

9. Render, follow up and cause to apply, with out prejudice to the power vested to Ethiopian roads Authority pursuant to proclamation No80/1998, the Design, Construction and Inspection activities of the Rural Roads to the international foreign contractors and consultants.

10.በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ. የገጠር መንገድ ግንባታ ወይም ጥገና በራሱ ኃይል ወይም በጨረታ የሚከናወንበትን አማራጭ እያጠና ለምክር ቤቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

ለ.ለገጠር መንገዶች ግንባታ፣ ጥገና፣ ፊዚቢሊቲ ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር እንደአግባብነቱ የሚያስፈልጉ አማካሪ መሐንዲሶች የሚመረጡበትን ሁኔታ ይወሰናል።

10. With out prejudice to the provisions of sub article 9 of this article:

A. Study and submit to the executive committee for approval, its recommendation concerning the construction or maintenance of rural road with its own force or through contractors.

B. Decide the conditions of selecting consulting engineers, as the case may be, required for the construction, maintenance, feasibility study, design and supervision in respect of Rural Roads.

11.የኮሚኔቲ መንገዶችን በሚመለከት ያስተባብራል የቴክኒክ አገልግሎት ይሰጣል።

11.Coordinate and render technical services to the public with respect to community roads.

12. የገጠር መንገድም ሆነ የኮሚኒቲ መንገድ ግንባታ አስተማማኝ የመንገድ ጠገና ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው ወይም ብቁ የጥገና ኃይል ኖሯቸው እንዲሠሩ መመሪያ በማዘጋጀት

12.Prpare and submit directives to the regional council by which both the rural and community road are to be carried out based on effective road maintenance plan or

- 309

በክልሉ ምክር ቤት ሲጸድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

13.ገጠር መንገዶችን በሚመለከት የማቴሪያል ጥናት ያካሂዳል፣ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ ይውላል።

14.ለገጠር መንገዶች ልማትና ጥገና የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጠን ያደርጋል።

15.የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንን በማማከር ገጠር መንገዶችን በሚመለከት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይንም መሣሪያዎችን ዲዛይን ይሠራል፣ በገጠር መንገዶችም ላይ ያኖራል።

16.የተሽከርካሪ ክብደትና መጠን ደንቦችን በገጠሩ መንገዶች ላይ ያስፈጽማል።

17.ገጠር መንገዶችን ከጉዳትና አግባብ ካልሆነ አጠቃቀም ይጠብቃል፣ በገጠር መንገዶች የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ያስወግዳል፣ እንዲወገዱ ያደርጋል።

18.ከገጠር መንገዶች ግራና ቀኝ እንዲሁም በአካባቢው ለሥራው የሚያስፈልገውን የመሬት መጠንና ሌሎች ሰዎች በዚሁ መሬት የሚጠቀሙበትን ሁኔታዎች በማቅረብ ያስወስናል።

19.ለገጠር መንገዶች ግንባታና ጥገና እንዲሁም ለመኖሪያ፣ ለመሣሪያ ማሳረፊያና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች ያለ ክፍያ ይጠቀማል፣ ሆኖም

ሀ.በዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም ምክንያት ከመሬቱ ለተፈናቀለ ለማንኛውም ህጋዊ የመሬት ባለይዞታ አግባብ ያለው ወረዳ ወይም የዞን መስተዳድር በተቻለ መጠን ምትክ መሬት ይሰጠዋል፣ በተጨማሪም በሚጠቀምበት መሬት ላይ ለሚገኙ ንብረቶች ባለሥልጣኑ በሕግ መሠረት ካሣ ይከፍላል።

ለ.ተፈናቃዩ አርሶ አደር ከሆነና በወቅቱ ምትክ መሬት ያልተገኘለት መሆኑን አግባብ ያለው የወረዳ ወይም የዞን መስተዳድሩ ሲያረጋግጥ መሬቱ በተገኘ ጊዜ ሊያገኝ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በመሬቱ ላይ ሰብል ቢኖርም ባይኖርም ባለሥልጣኑ አርሶ አደሩ ከመሬቱ ላይ ባይፈናቀል ኖሮ ሊያገኝ ይችል የነበረውን የተወሰነ ገቢ

maintenance man power. And up on approval fallow up its implementation.

13.Study or cause the study of materials concerning rural roads and apply there of useful results.

14.Train or cause the training of manpower necessary for development and maintenance of Rural Road.

15. Design, in consultation with the Ethiopian Roads Authority, Traffic Control Posts and Devices relating to rural roads and place same on rural roads.

16.Enforce vehicle weight and size regulations on Rural Roads.

17.Protect Rural Roads from damage and abuse remove and cause the removal of obstructions from Rural Roads.

18.Submit for approval the extent of land required for its activities in the adjacency as well as surrounding of Rural Roads and the conditions of use of such land by others.

19. Use free of charge, Land and such other resources and quarry substances required for the purpose construction and maintenance of Rural Road and camp, storage of equipment and other required services; provided, however,

a) A substitute land shall be given to a legal possessor removed from his land because of the execution of this article, in addition the authority shall pay compensation in accordance with law for any property found on the land.

b) Where the evicted person is a farmer and at that time where the appropriate woreda or zonal administration have ascertained that substitute land for the farmer was not found, with out prejudice to his right of getting substitute land when available, the authority shall pay the necessary compensation the farmer may get if he was not removed, weather there is agricultural

ተገምቶ የመፈናቀያ ካሣ ይከፍላል፣
ሐ.ዝርዝር አፈጻጸሙ የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

20.ማንኛውም ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ለልዩ ወይም ለጋራ ዓላማና አገልግሎት የሚሠራውን የሚጠግንውንና የሚያስተዳድረውን መንገድ ይመዘግባል፣

21.ስልጣንና ተግባሩን በሥራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ አካባቢው እንዲጠበቅ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ያደርጋል፣

22.ስልጣንና ተግባሩን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ለሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል።

10. <u>የዋናው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

ዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ላይ ለባለስልጣኑ ከተሰጠ ት ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1.የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

2.በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 42/1985 መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል።

3.ባለሥልጣኑ በሥራው አፈጻጸም የሚመራባቸውን ውስጠ ደንቦችና መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ በቦርዱ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

4.የባለሥልጣኑን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን፣ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራሞችንና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

5.በጸደቀ የባለሥልጣኑ ፕሮግራሞችና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

6.ተጠሪነታቸው ለዋናው ሥራ አስኪያጅ የሆኑ የባለሥልጣኑን መምሪያ ኃላፊዎች መርጦ ለቦርዱ ሹመት ያቀርባል፣

7.የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

8.የባለሥልጣኑን የሥራ አፈጻጸም፣ የሂሣብ መግለጫዎችና የእዲት ሪፖርቶች በየወቅቱ

production or not in his land.
c. the implementations shall be determined by directives made by the regional executive committee.

20. Register the road constructed maintained and administered by any physical or juridical organization for special or common objective and service.

21. Take necessary means to protect the environment on the implementation of its powers and duties.

22. perform such other activities necessary for the execution of its powers and duties

10. Powers and Duties of the General Manager

The General Manger being accountable to the board and Executive committee of the Region; shall, in addition to the powers and duties vested in the Authority as enumerated under article 9 of these proclamation, have the following powers and duties to:

1.Direct and administer the activities of the authority

2. Employ, administer, promote and dismiss its employees in accordance with the labour proclamation No. 42/1993.

3.prepare and submit to the board internal regulations and directives, guiding the Authority. And upon approval implement the same.

4.Prepare and submit to the board short and long term plan, annual work programs and budget of the authority; and upon approval supervises the implementation of the same.

5.Effect expenditure, in accordance with the approved budget and plan of action of the authority.

6.Submit to the board the appointment of those department heads, which are accountable to the General Manager.

7.Execute and cause the execution of the decision of the board.

8.Prepare and submit to the board activity performances, financial explanations and audit

311

ለቦርዱ ያቀርባል፣
9.ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑ ይወክላል፣
10.አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቦርዱን በተለይ በማስፈቀድ ክርክሮችን ከፍርድ ቤት ወጪ መፍታት ይችላል፣
11.ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ የሥራ ኃላፊዎችና ለሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም እርሱን ተክቶ ከ30 ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ኃላፊ ሲወከል ውክልናው በቅድሚያ ለቦርዱ ቀርቦ መጽደቅ አለበት።

ክፍል አምስት
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

11. የገንዘብ ምንጭ

የባለሥልጣኑ ገቢ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፣
1. የክልሉ ምክር ቤት የሚመድበው በጀት፣
2. የመንገድ ፈንድ እና
3. ሌሎች ምንጮች

12. የሂሣብ መዛግብትና አዲት

1.ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2.የባለሥልጣኑ ሂሣብና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና አዲተር ወይም በሚሰይመው ሌላ አዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

13. የቴክኒክ ምርመራ

1.የቴክኒክ ምርመራ በእያንዳንዱ የግንባታና ጥናት ሥራዎች ላይ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይከናወናል።

14. የተሻሩ ሕጎች

1.የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ የገጠር መንገዶች ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.7/1988 በዚህ አዋጅ ተሽሮ ተተክቷል።

2.ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

15. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጳጉሜ 2 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ባህር ዳር
ጳጉሜ 2 ቀን 1991 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

reports of the authority.
9.Represent the authority, in its dealings with other third parties.
10. Settle disputes out of court with the specific permission of the board as may be necessary.
11.Delegate parts of his powers and duties to the officials and other employees of the authority, to the extent necessary for the efficient management of the authority. However that the delegation of an official who acts on his behalf for more than 30 days requires prior approval of the board.

PART FIVE
Miscellaneous Provisions

11. The Budget

The budget source of the authority shall be allocated from the following source:
1.The budget allocated by the Regional council.
2. the road fund
3. Other sources.

12. Financial Records and Audit

1. The Authority shall keep proper and complete financial records
2. The finances and financial documents of the authority shall be, audited annually by the auditor General or external auditors.

13. Technical Auditing

1.Technical auditing shall be conducted in each construction and study activities at least once in a year.

14. Repealed laws

1.Aproclamation to provide for the establishment of Rural Roads Authority of the Amhara National Regional state No 7/1999 is repealed and replaced by this proclamation.
2. Any Law that is in consistent with this proclamation shall not apply to matters provided for in this proclamation.

15. Effective Date

This proclamation shall come into force as of 7th day of September 1999.

Done at Bahir Dar
This 7th Day of Sept. 1999.
Council of The Amhara National Regional State.